# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ 10ኛ ጠቅላላ

## ጉባኤ የአቋም መግለጫ

እንደሚታወቀው ሁሉ ኢሕኤዴግ ሀገራችን ድህረ-ደርግ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እንደምትገነባ ቃል ገብቶ አዋጅ አውጆ ለዓለምና ለሕዝባችን ምሎ ተገዝቶ በመንገር ጉዞ ከተጀመረ እነሆ ሃያ ሦስት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በነዚህ ሃያ ሦስት ዓመታት በመጀመሪያዎቹ የተስፋ ዓመታት የዲሞክራሲ ጭላንጭል ከመታየቱ በቀር የተናፈቀው የመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እውን ሊሆን አልቻለም፡፡ ይልቁንም በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ብልጭ ብለው የነበሩት የፕሬስ ነፃነት፣ የመጻፍ ነፃነት፣ የሚዲያ ሕዝባዊ አገልግሎት የመሳሰሉት ተደፍጥጠው ዛሬ ከዕይታ ተወግደዋል፡፡ ዛሬ በመንግስት ሚዲያ የኢሕአዴግን ፕሮፓጋንዳ ከሞስማት በቀር ሌላ አማራጭ በዚህ አገር የለም፡፡ በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ውስብስብ በሆነ የሀገራችን የፖሊቲካ ሁኔታ ውስጥ ታግሎ ሕዝባችንን ለማታገል ከብዙ ምክክርና ውይይት በኋላ የተፈጠረው የዛሬው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ በፖለቲካ አጋምና ቀጋ የታጠረውን መንገድ እያለፈ እነሆ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ መድረክ ባሳለፋቸው የትግል ዓመታት ከገዥው ፓርቲ በአባለቱና በደጋፊዎቹ ላይ የደረሰውና እየደረሰ ያለው አፈና ፣ ወከባ፣ እስር እና ግዲያ ሳይበግረው ይበልጥ እየተጠናከረ በመምጣት እነሆ ዛሬም አስረኛ ጠቅላላ ጉባኤውን በተሳካ ሁኔታ አካሂዶ በሀገራችን ወቅታዊ ፖለቲካዊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በስፋትና በጥልቀት ከመከረ በኋላ ማኒፌስቶ በማፅደቅ አጠናቋል፡፡ የሚከተለውንም የአቋም መግለጫ አውጥቷል፡፡

1. ቀደም ሲል መድረክ በተደጋጋሚ ስለ ሀገር ጉዳይ ከገገርው ፓርቲ ጋር ለመወያየት ያቀረባቸው ጥያቄዎች ተገቢና ዛሬም ወቅታዊ በመሆናቸው ኢሕኤደግ ይህንን ጥያቄ በሀገራዊና ንጹሕ ኅሊና ተመልክቶ ውይይቱ እንዲካሄድ እንዲያደርግ፡፡
2. በሀገራችን በየ አምስት ዓመታቱ የሚደረጉ ምርጫዎች ከውዝግብ ነፃ ሆነው የተካሄዱበት አንድም ጊዜ የለም፡፡ለዚህም ትልቁ ችግር የምርጫ ቦርድ የማስፈጸም አቅም ማጣትና ወገንተኝነት ነው፡፡ ዘንድሮም ምርጫው የሚካሄድበትን ሠሌዳ ምርጫ ቦርድ አያወጀ ነው፡፡ ይኸንን ምርጫ ለማካሄድ ቦርዱ በተደጋጋሚ በመድረክም ሆነ በሌሎች ታቃዋሚ ፓርቲዎች የተጠየቀውን ጥያቄዎች ወደ ጎን ትቶ ወደ ምርጫ ከመሮጥ በፊት በአግባቡ እንዲመልስ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

መድረክ
FORUM

3. ኢሕአዴግ ለእኔ ታማኝ ካልሆናችሁ በማለት ለሀቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ነፍጐ ለታማኞቹ የሚረጨውን የሕዝብ ገንዘብ ማካፋል አቁም ለሁሉም ፓርቲዎች በፍትሕዊነት እንዲከፋፈል እንዲደረግ ::

4. የሀገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሀገር ሲባል በጋራ የሚሠሩ ብዙ ጉዳዮች መኖራቸውን ተገንዝበው የጋራ አሠራሮችን በመፍጠር አንድ ላይ ቆመው ይኸንን አመባገነን ስርዓት ለመተካት የሚጠበቅባቸውን ሁሉ እንዲወጡ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

5. ዛሬም ተቃዋሚ የፓለቲካ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ላይ ተባብሶ የሚካሄደው ወከባ ፣ እስራት፣ ማሳደድና ግዲያ ባስቸኳይ ቁሞ ቢሮዎቻችንን ከፍተን ሕዝባችንን በተገቢውና በሕጋዊ መንገድ እንድንገናኝ ኢህአዴግና መንግስት ለየክልሎቹና ለበታች አካላቶቻቸው ጥብቅ መመሪያ እንዲሠጡ፡፡ ለዚህም የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተገቢውን ድርሻቸውን እንዲወጡ አበክረን እንጠይቃለን፡፡

6. በኦሮሚያ ውስጥ አዲስ አበባንና በዙሪያዋ የሚገኙ ከተሞችን በልማት ለማስተሳሰር ወጣ በተባለው ማስተር ፕላን ላይ ለቀረበው ተቃውሞ መንግስት በወቅቱ ምላሽ ባለመስጠቱ የሕይወትና የንብረት ጥፋት ደርሷል፡፡ለዚህ ድርጊት ተጠያቂ የሆኑ ሰዎች ለፍርድ ባስተኳይ እንዲቀርቡ ሆኖ ሕይወታቸውን ላጡና ንብረታቸውን ለወደመባቸው ዜጐች ቤተሰቦች መንግስት ካሳ እንዲከፍል ::

7. የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች ጦማሪያንና ብሎገሮች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ እንዲፈቱ ::

8. መንግስት ከሕገ-መንግስት አግባብ ውጪ በየወቅቱ በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ እየገባ ሁከቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡ ስለሆነም መንግስት ከዚህ ድርጊቱ እንዲታቀብና በዚህ ሠበብ የታሠሩ ሙስሊም ወገኖቻችን ባስቸኳይ እንዲፈቱ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

9. ዛሬ ሀገራችን በከፍተኛ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ የምትገኝ በመሆኑ ለነዚህ ጥያቄዎቻችን ተገቢው ምላሽ ባፋጣኝ እንዲሰጠን እየጠየቅን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ረገድ ለምናደርገውም ትግል ሆነ ለአጠቃላይ ሁለንተናዊ ትግላችን በዕውቀት በሀብትና በጉልበት ከጎናችን እንዲቆሙ ሀገራዊና ታሪካዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

አዲስ አበባ ጥቅምት 29/2007 ዓ.ም

መድረክ
FORUM